# ለመዋእለ ህፃናት ዝግጅት፡-

## ሊተርሲ ወላጆች ማድረግ የሚችሉት

በቤት ውስጥ በሚነገር ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች የተለያዩ ተግባራት ሊከናወኑ ይችላሉ።

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Maryland

### የንግግር ቋንቋ እና ቃላት



- በየእለቱ ስለሚከናወኑ ተግባሮችና ተሞክሮዎች ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ።
- ከልጅዎ ጋር መጽሐፍት አንብቡ እና ስለ ታሪኩ ወይም መረጃው ተነጋገሩ።
- ልጅዎን ጥያቄዎች ይጠይቁ።
- ልጅዎ ለሚጠይቃቸው/ለምትጠይቋቸው ጥያቄዎች መልስ ይስጡ።
- ልጅዎ በአረፍተነገሮች እንዲናገር/እንድትናገር አበረታቱ።
- ልጅዎ ከሌሎች ልጆች ጋር እንዲጫወት/እንድትጫወትና እንዲነጋገር/እንድትነጋገር ያበረታቱ።
- ነገሮች ምን እንደሚመስሉ፣ እንደሚሸቱ፣ እና ምን አይነት ስሜት እንደሚሰጡ ተነጋገሩ።
- ልጅዎ አዳዲስ ነገሮችን እንዲያደርግ/እንድታደርግ እና እንዲያይ/እንድታይ እድሎችን ይፍጠሩ። ሠፈር ጎረቤት አካባቢ በእግር መንዝ/Go for walks፣ የዱር እንስሳት የሚገኙበት ቦታ መነብኘት፣ ቤተመጻሕፍት፣ እና ሌሎች የሚያስደስቱ ቦታዎችን ጉብኝት አድርጉ።
- ለልጅዎ ስዕል ለመሳል፣ ለመደነስ፣ ሙዚቃ ለመስማት፣ እና ሙዚቃ ለመጫወት እድሎችን ይስጡ። ስለሠራ(ች)ው ሥራ ተነጋገሩበት።
- ልጅዎ እየሠራ(ች) ልምድ የሚያገኝበትን/የምታገኝበትን እድሎች ማመቻቸት አለብዎት። ለምሳሌ:-አንዳንድ ነገሮችን በመነካካት፣ ለማዳ የቤት እንስሳትን፣ ጥቃቅን ተዋህሳን፣ ምግብ በሚያበስሉበት ጊዜ እንዲያግዝ/እንድታግዝ ማድረግ፣ ምግቦችን በማሽተት ጣዕም እንዲለይ/እንድትለይ ማድረግ፣ ትናንሽ መኪናዎች እና የጭነት ተሽከርካሪዎችን ማሳየት ወዘተ
- ልጅዎን ቀላል መመሪያዎችን እንዲከተል/እንድትከተል ይጠይቁ፣ ልጅዎ ብዙ ነገሮችን የሚችለውን/የምትችለውን ያህል ራሱን ችሎ እንዲሠራ/ራስዋን ችላ እንድትሠራ ያደፋፍሩ፤ ለምሳሌ፡- ልብስ መልበስ፣ ጠረጴዛ ማስተካከል፣ ወይም ቁርስ ማዘጋጀት ወዘተ።

### ስለ ህትመት ፅንሰ ሀሳቦች






#### ከልጅዎ ጋር እያነበቡ

- የሽፋን ገጹን እያመለከቱ ርእሱን ያንብቡ።
- ሽፋኑ ላይ ስላለው ስእል ተነጋገሩ።
- ታሪኩ የሚጀምርበትን እና የሚያልቅበትን ያመልክቱ።
- ልጅዎ ገጹን በመገልበጥ እንዲረዳ/እንድትረዳ ያድርጉ።
- አዲስ ገጽ ለማንበብ ሲጀምሩ፣ ታሪኩ ከየትኛው ቦታ እንደሚቀጥል ያመልክቱ።
- ጣትዎን ከቃላቶቹ በታች በማንቀሳቀስ ቃላቶችን ይከተሏቸው።
- እርስዎ እያነበቡ ልጅዎ በቃላቶቹ ሥር እየተከታተለች/እየተከታተለ ከሥር ጣቱን/ጣቷን እንዲያንቀሳቅስ/እንድታንቀሳቅስ ያደፋፍሩ

### የድምፅ ንግግርን በንቃት መከታተል

- ቤት የሚመቱ መዝሙሮችን ከልጅዎ ጋር ዘምሩ።
- የህፃናት ግጥሞችን ከልጅዎ ጋር በቃል አንብቡ። ሲያነቡ፣ ከሚገጥም ቃል/ስንኝ በፊት ቆም በማለት ልጅዎ ክፍተቱን እንዲሞላ/እንድትሞላ ያበረታቱ። ለምሳሌ:- Humpty Dumpty sat on a wall. Humpty Dumpty had a great ______.
- በቤትዎ ዙርያ በሚታዩ ነገሮች ላይ በማመልከት ስማቸውን ይጥሩ። ለምሳሌ:- ኳስ ከዚያ ልጅዎን ቤት የሚመታ/የሚገጥም ቃል/ስንኝ እንዲናገር/እንድትናገር ይጠይቁ ለምሳሌ:- tall, call, fall, wall.
- cat፣ dog፣ እና sat የመሳሰሉ ሶስት ቃላትን ይናገሩና የትኞቹ ስንኞች እንደሚገጥሙ ልጅዎን ይጠይቁ(ቋ)ት።
- ከልጅዎ ጋር ትርጉም-የለሽ የምላስ ድምፀት በማሰማት ተነጋገሩ። ለምሳሌ:- Peter Piper picked a peck of pickled peppers.
- ልጅዎ በተመሳሳይ ድምፅ በሚጀምሩ በርካታ ቃላት ትርጉም-የለሽ ድምጾችን ፈጥሮ(ራ) እንዲናገር/እንድትናገር አግዙ(ዟ)ት። ለምሳሌ:- Betty bought a big, blue balloon.

## ሆሄያት/የፊደላት ግንዛቤ

- Alphabet Song (የፊደላት መዝሙር) ከልጅዎ ጋር አብራችሁ ዘምሩ።
- ልጅዎ ከአጠገብዎ ተቀምጦ/ተቀምጣ፣ የልጅዎን ስም በወረቀት ላይ ይፃፉና የጻፏቸውን ፊደላት ስም አንድ በአንድ ይጥሩ።
- ልጅዎ ስሙ(ሟ)ን እየጠራ(ች) እንዲጽፍ/እንድትጽፍ ይርዱ በመጀመሪያ ልጅዎ ጥቂት ፊደላትን ብቻ ሊጠቀም/ልትጠቀም ይችል/ትችል ይሆናል ለምሳሌ:- Jenny ተብሎ መፃፍ ያለበትን ስም JNY በማለት ይጽፍ/ትጽፍ ይሆናል።
- ከልጅዎ ጋር በመሆን፣ የልጅዎን ክፍል ስም ጽፈው ምልክት ያድርጉበት።
- በማስታወቂያዎች፣ በምግብ እቃዎች፣ ለምሳሌ:- cereal boxes፣ የምግብ ዝርዝር የተጻፈባቸው እቃዎች፣ እና በመጽሔቶች ላይ ያሉትን የእያንዳንዱን ፊደል ስም እያሳዩ በስም ለይተው ይጥሩ።
- ለልጅዎ ABC መፃህፍት አንብቡ።
- ለልጅዎ ከአንድ መፅሔት አንድ ገፅ ይስጡ። በገጹ ላይ ያለውን ፊደል ይክበቡት እና ልጅዎ ተመሣሣይነት ያላቸውን ፊደላት እንዲያከብ/እንድታከብ ያድርጉ




## የቃላት ግንዛቤ

- ከልጅዎ ጋር አብረው መጽሐፍት ያንብቡ የተለመዱ ቃላትንም ያመልክቱ።
  ለምሣሌ:- the, I, go, a, and, see, like, me, you.
- ማቀዝቀዣ/ረፍሪጂሬተር ላይ የፊደል ማግኔቶችን ያስቀምጡ። ልጅዎ ቀላል ቃላትን እንዲሰራ/እንዲድትሰራ ያበረታቱ።
  ለምሣሌ:- cat, dog, mom, dad.

## ድምፅ (Phonics)

- ስእሎችን ወይም እቃዎችን ይመልከቱ። የስዕሉ ወይም የእቃው ስም የሚጀምርበትን ድምፅ ልጅዎ እንዲናገር/እንድትናገር ይጠይቁ(ቋ)ት። በዚያው ድምፅ የሚጀምር ሌላ ስእል ወይም እቃ ልጅዎ እንዲያመለክት/እንድታመለክት ያድርጉ።
- አንድ ታሪክ ወይም አፀደህፃናት የሚገጥም ቃል እያነበቡ ልጅዎ እያዳመጠ/ እያዳመጠች በተመሣሣይ ድምጽ የሚጀምሩ ቃላትን እንዲናገር/እንድትናገር ያድርጉ።
  በዚሁ ዓይነት በተመሣሣይ ድምፅ የሚጀምሩ ሌሎች ቃላትን እያሰበ(ች) እንዲናገር/እንድትናገር ያድርጉ።
- በፊደላት ጨዋታዎችን ተጫወቱ። ለምሳሌ:- በ M ፊደል የሚጀምር አንድ ነገር እሰልላለሁ።
- ሆሄያትን ብጣሽ ወረቀት ላይ ይፃፉ እና በአንድ የወርቀት ከረጤት ውስጥ ያስገቡ። ልጅዎ ከከረጢት ውስጥ ወረቅት እንዲያወጣ/እንድታወጣ እና የፊደሉን ስም እና ድምፁን ለይቶ/ለይታ እንዲናገር/እንድትናገር ያድርጉ በመቀጠል ልጅዎ በተመሣሣይ ድምፅ የሚጀምር ቃል እንዲናገር/እንድትናገር ያድርጉ።
- ፊደላትን ከመጽሔቶች ላይ በመቁረጥ ወይም ስእሎችን በመሣል ልጅዎ የፊደል ገበታ እንዲሠራ/እንድትሠራ ይርዱ።
- ልጅዎ ፊደላትን እና ስማቸውን በመጻፍ እንዲዝናና/እንድትዝናና ያድርጉ። ልጅዎ የጻፈውን/የጻፈችውን እንዲያሳይ/እንድታሳይ ያድርጉ ልጅዎ ለመፃፍ ያደረገ(ች)ውን ያሣየ(ች)ውን ትጋት ያድንቁለ(ላ)ት።

**የንባብ መርጃዎችን እና ምክረሃሳቦችን ለማግኘት እባክዎን የአካባቢዎን የህዝብ ቤተ-መጽሐፍት ይጎብኙ።**
www.montgomerycountymd.gov/library

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
ሕትመት:- በ Department of Materials Management for the Elementary Integrated Curriculum Team
0556.24 • Editorial, Graphics & Publishing Services • 1/24 • 1,450
Copyright © 2024 Montgomery County Public Schools, Rockville, Maryland

